# ዓባይ፣ ግብፅ፣ ሻዕቢያ እና "ሶስተኛው ምላሱ"

ማህደር አለባቸው 04/28/13

(ክፍል ሁለት)

ውድ አንባቢዎቼ በክፍል አንድ ፅሑፌ ላይ ሻዕቢያ በአንድ ራስ ሶስት ምላስ አብቅሎ በዓባይ ጉዳይ ላይ የደሰኮራቸውን የተምታቱ ሃሳቦች አስነብቤያችሁ ነበር። በተለይም "በሶስተኛው ምላሱ" አማካኝነት "የግብፅን ታሪካዊ የውሃ ባለቤትነት እንደግፋለን" በማለት ሰሞኑን የጀመረውን ሽር ጉድ መሠረተ-ቢስነት በስፋት እንደምንቃኘው ቃል ገብቼ ነበር፡፡ እናም የአስመራው አስተዳደር "ሶስተኛው ምላስ" እንዲህ ይቀጥላል።...መልካም ንባብ።

የኤርትራ መንግሰት የፀረ-ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት መዝሙር አቀንቃኝ ነው። አቀንቃኝ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የታቻለውን ሁሉ አድርጓል፡፡ የተቻለውን ብቻ ሳይሆን ከሚችለውም በላይም ተግቶ ሰርቷል፡፡ እየሰራም ነው፡፡ ወደፊትም መስራቱ አይቀርም። ትርፉ ውድቀቱን ማፋጠን እንጂ ኢትዮጵያዊነትን ባያመክንለትም የጥፋትን ብልሃትና መልኩን እየቀያየረ ዛሬም ድረስ እንደ ፍጥርጥሩ እንዳለ አለ፡፡

ጦር ሰባቂው አቶ ኢሳያስ በተዘዋዋሪ መንገድ "ዓባይ የኢትዮጵያ አይደለም" እያሉ ነው፤ ለፕሬዚዳንት ሙርሲ የላኩት ደብዳቤ ሲተረጎም፡፡... ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ኤርትራና ግብጽ ሰሞኑን አብረው ለመስራት የሁለትዮሽ ስምምነት (bilateral relation) ማድረጋቸው አይከፋም። አብሮ በሰላም መስራት ፋይዳው የበዛ በመሆኑ የሁለቱ ሀገራት ውይይትና ስምምነት በጄ በተባለ ነበር– ውስጡ ፀረ- ኢትዮጵያ ህዝብነት ተሸረበበት እንጂ፡፡ ሁለቱ ሀገሮች ከተመካከሩባቸው (መመካከር ከተባለ) ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የናይል ወንዝ ነው፡፡ ውድ አንባቢዎቼ! በክፍል አንድ ፅሑፌ ላይ እንደምታስታውሱት፤ አቶ ኢሳያስ በአማካሪያቸው በአቶ የማነ ገብረአብ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው በአቶ ኡስማን ሳላህ አማካኝነት ለግብጽ ፕሬዚዳንት ሙርሲ የላኩት ደብዳቤ ፀረ- ኢትዮጵያዊነት የተንጸባረቀበት መሆኑን ገልጬ ነበር፡፡ ኤርትራ ግብፅን ለክፍለ ዘመናት ብቸኛ ተጠቃሚ የሚያደርጋትን ህግ የሚደግፍ መሆኑን እንደሚገልፅም ጭምር– የአቶ ኢሳያስ መልዕክት። ፕሬዚዳንት ሙርሲ በበኩላቸው ኤርትራ በናይል ጉዳይ የግብጽ "አጋር" ሆና በመቆሟ ደስተኛ መሆናቸውን አስታውቀዋል። በአጭሩ ተደናንቀዋል ማለት ሳይሻል የሚቀር አይመስለኝም። ከዚህ በተጨማሪም ግብፅ ከአቶ ኢሳያስ ጋር ጊዜ ሳትውስድ ለመምክር ፍላጎት እንዳላት መነገሩም ተዘግቧል፡፡

ሁላችንም እንደምንገነዘበው የአቶ ኢሳያስ ሱስ ሃቅን ድጦ ውሸትን ማንገስ ነውና ከግብጽ ጋር በትብብር ለመስራት ደፋ ቀና ማለታቸው በየትኛውም ዲፕሎማሲያዊ ስሌት ተቀባይነት የለውም። በተለይም ነባሩንና የናይል ተፋሰስ ሀገሮችን ሙሉ በሙሉ የበይ ተመልካች የሚያደርገው የቅኝ ገዥዎች ህግን (ህግ ከተባለ ማለቴ ነው) ደግፎ መቆም ማለት አንድም የላይኛውን የተፋሰስ ሀገራትን መናቅና የህዳሴውን ግድብ ግንባታ መቃወም ተደርጎ የሚወሰድ ነው— ነባሩ የቅኝ ገዥዎች ህግ ኢ-ፍትሐዊ ነውና፡፡

በእርግጥ አቶ ኢሳያስ መልክተኛ ካይሮ ድረስ ልከው ከግብፅ ጋር በጋራ ለመስራት መሞከራቸው ባልከፋ ነበር፡— ድብቅ አጅንዳው ፀረ - ኢትዮጵያዊነቱን የሚያፋፍምበት ሚዳ ለማፈላለግ ሆነ እንጂ፡፡ እንደሚታወቀው አቶ ኢሳያስ የልማት፣ የሠላምና የዴሞክራሲ አጀንዳ የላቸውም፡፡ እናም ወደ ግብፅ የተጓዙት ለልማት ወይም ለሁለትዮሽ ትብብር እንዳልሆነ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሰውዬው ከሳህል ተራራዎች ጀምሮ መንግስት እስከሆኑበት ድረስ ስለ ልማት፣ ስለ ሰላምና ስለ ዴሞክራሲ መስማት የሚፈልጉ እንዳልሆኑ የኋላውና አሁን ያለው የሁከት ድርሳናቸው በገሃድ ስለሚናገር ነው፡፡ በመሆኑም የሰውዬው ሰሞነኛው ቀመር ያው የተለመደውን ፀረ - ኢትዮጵያ ህዝብ አቋምን ማቀንቀን ነው—"የጠላቴ ጠላት ለኔ ወዳጄ ነው" ዓይነት ጊዜው ያለፈበት አሮጌ ተረት፡፡

የሻዕቢያው ቁንጮ በደብዳቤም ቢሆን ወደ ግብፅ ያማተሩት ኢትዮጵያና ግብፅ በደም የሚፈላለጉ የሁል ጊዜ ጠላቶች ናቸው የሚል 'ጦር አውርድ' ቀመራቸውን አስልተው ነው። እርግጥ እኔም ሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ ወይም ኩታ ገጠም ጠላቶች ናቸው እያልኩ አይደለም፡፡ ሀገራቱ ኢትዮጵያዊውን ዘመናትን የተሻገረ የባህል፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ ትስስር እንዳላቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም። በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሁለቱ ሀገራት የሁለትዮሽ ትብብር እየጎለበተ መጥቷል፡፡... ይህ ማለት ግን የማያግባቡን ጉዳዮች አልነበሩም ማለት አይደለም፡፡ ሁሉም ሀገራት በሁሉም ጉዳዮች አይግባቡም፤ በሁሉም ጉዳዮችም አይስማሙም፡፡ የሚያቀራርባቸው ብሔራዊ ጥቅሞች የመኖራቸውን ያህል፣ የማይስማሙባቸውም ቢኖሩ አይገርምም፡፡ ይህ ሃቅ የዘመናዊው ዓለም የሁለትዮሽ ተግባቦት (Two-way Communication) ነባራዊ ዕውነታ ነውና።

እናም ኢትዮጵያና ግብፅ በአባይ አጠቃቀም ዙሪያ ለዘመናት ሳንግባባ መኖራችን እውነት ነው፡፡ አለመግባባት ደግሞ የጠላትነት መለኪያ አይደለም፡፡ ግብፅ ለዘመናት ብቸኛ ተጠቃሚ የሚያደርጋትን አሮጌውን የህግ ማዕቀፍ ደንግጋ በዓባይ ወንዝ የመጠቀም መብታችንን መንፈጓ የትናንት ሃቅ ነው— ጠላታችን ናት ባንልም፡፡ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚረዳው ሀገራችን ኢትዮጵያ 85 በመቶ ያህሉን የናይል ወንዝ ድርሻ የምታበረክት ታላቅ ባለ ይዞታ ብትሆንም ቅሉ፤

ከወንዙ አንዳችም ጥቅም ጠብ ሳይልላት ትውልዶችን በበይ ተመልካችነት ተሻግራለች፡፡ ዓባይን እንዳሻቸው ሲበሉትም ሆነ ሲጠጡት የኖሩት ግብጽና ሱዳን ናቸው– “ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል” እንዲሉ፡፡

ሁለቱ ሀገራት በተለይም ግብፅ በዓባይ ወንዝ የመጠቀም መብታችንን በተለያዩ መንገዶች ስትጋፋ መኖሯ አይታበይም፡፡ ምንም እንኳን በታሪካችን ዓባይን ለመገደብ የተነሳ ትውልድ ኖሮ በግብፅ እምቢተኝነት ሳቢያ ከልማት ባይስተጓጎልም፤ በእጅ አዙር ጥረቶችን ታመክን እንደነበር የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በወቅቱ እንደ ቡጥሮስ ቡጥሮስ ጋሊ ያሉ ተፅዕኖ ፈጣሪ ግብፃውያን፤ እንኳንስ ዓባይን መገደብ ቀርቶ ስለ አባይ ማሰብ እንዳንችል ጉዳዩን በእሾህ ማጠራቸው አይዘነጋም፡፡ ታዲያ ጊዜያት አልፈው ጊዜያት ሲተኩ ያንን እ.ኤ.አ በ1929 እና በ1959 የተረቀቀን ያረጀ ያፈጀና ኢ- ፍትሐዊ ብቻ ሳይሆን ኢ- ሞራላዊ ህግን በመቀየር ሁሉንም የተፋሰሱ ሀገራት እኩል ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የውሃ ህግ ለመደንገግ የሀገራችን ድርሻ የአንበሳው ያህል ነው፡፡ ምስጋና ለራሳቸው ምቾትና ድሎት አንድም ቀን ሳያስቡ ሌት ተቀን ሰርተው ይህን ዕውን ዕውን ላደረጉት ለታላቁ መሪያችን ለአቶ መለስ ዜናዊና ለድርጅታቸው ይግባቸውና።… እናም ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የዚህ እልህ አስጨራሽ ጥረት ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ታዲያ የሻዕቢያው ፊታውራሪ አሮጌውን የናይል ወንዝ አጠቃቀም “ህግ” በመደገፍ ከግብፅ ጎን መቆማቸን ሲገለፁ፤ አንድም የህዳሴውን ግድብ ግንባታ እየተቃወሙ ነው፣ ከፍ ሲልም የተፋሰሱ ሀገራት የተስማሙበትን ህገ- ደንብ የሚቃወም በመሆኑ ፀባቸው ከሁሉም የራስጌው የተፋሰሱ ጋር እንደሆነ ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል። ለነገሩ የአቶ ኢሳያስ የኋላ ታሪክ ሲፈተሽ ፀረ - ኢትዮጵያዊነታቸው ይገዝፋልና ሃቁን በመደፍጠጥ ከግብጽ ጎን ለመቆም መውተርተራቸው የግብፅ ወዳጅ በመምሰል ወዳጅ ለማፈላለግ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሻዕቢያ በእኩይ ምግባሩ ከቀጣናውም ሆነ ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ የተገለለ በመሆኑ ባለማወቅ ከሚናውዙ ፀረ - ኢትዮጵያዊያን ጋር በመሰለፍ ለብቸኝነቱ ማስታገሻ እየፈለገ ነው። እርግጥም ለጊዜውም ቢሆን የአዞ እንባ እያነባ ሽርክ ቢያፈላልግ ብዙም እንግዳ ነገር አይደለም—በዚህ ዓይነት ቀቢፀ-ተስፋዊ ጉዞው እግረ መንገዱንም ቢሆን ለፀረ - ኢትዮጵያዊነት ሱሱ ሁነኛ አጋር አስሶ ሊያገኝ ይችላልና፡፡

ሁላችንም እንደምረዳው አቶ ኢሳያስ በመንግስትነት ከተደራጁ በኋላ ራሳቸውን ሾመው ብቅ ካሉበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያን የደም ምድር ለማድረግ ታግለዋል– ባይሳካላቸውም፡፡ ለራሳቸው የተሳሳተ ቀመር በማስላትና በጡንተኝነትም ሆነ በስልጣኔ የበላይንት ተሰምቷቸው ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግና በሀብቷ ተንጠላጥለው ለማደግ የቀበጡበት ጊዜም ነበር– ዕቅዳቸው ቅዥት እንደነበር እስከተገነዘቡበት ጊዜ ድረስ። እናም ልማታችንን፣ ሰላማችንንና የዴሞክራሲ ስርዓት

ባህል ግንባታችንን ሊያደናቅፉ አሊያም ሊስተጓጎሉ ያልፈነቀሉት ድንጋይ፣ ያልሞከሩት የጥፋት ወዳጅ አልነበራቸውም፡፡ መሰል አጋሮቻቸውንም እያሰለጠኑ ወይም እያሰየጠኑ ልከውብናል፡፡

ሰሞነኛው ድካማቸውም የነባር ዕቅዳቸው ተቀጥያ ነው– ፀረ - ኢትዮጵያዊነታቸው አገርሽቶባቸው። አዎ! ከዓለም ተገልለውና ኢኮኖሚያቸው ላሽቆ ተስፋ ቆርጠው በተቀመጠበት ሰዓት ግብፅ ትዝ አለቻቸው፡፡ ትዝ ብላቸውም የማያዋጣ ሂሳብ ቀመሩ፡፡ እናም ከግብፅ ጎን ተሰልፈው ፀረ - ኢትዮጵያዊነታቸውን ለማራገብና አቧራ ለማስነሳት ሮከሩ፡፡ ምንም እንኳን አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓችነታቸውን የማይረዳ የለምና ጠጋ ጠጋ ማለታቸው ያለ ምክንያት እንዳልሆነ ካይሮን ጨምሮ ሌሎች ሀገራት የሚረዱት ቢሆንም፡፡ በአንፃሩ ግን አቶ ኢሳያስ የሀገር ውስጥ ጉዳያቸው በልማት፣ በሠላምና በዴሞክራሲ ጥያቄዎች የታጨቀ ነው፡፡ የእርሳቸው መንግስት በማንኛውም ጊዜ በወታደሮች ሊቀለበስ የሚችል መሆኑም በገሃድ ታይቷል። ሰውዬው ግን እየተንገዳገደ የሚገኘውን መንግስታቸውን ከመታደግ እንዲሁም ስለ ኤርትራዊያን ህዝባዊ ጥያቄዎች ከማሰብ ይልቅ ዛሬም አሮጌ ሃሳባቸውን አንግበው ወደ ካይሮ መሮጥን መርጠዋል። የእርሳቸው አጀንዳ ኢትዮጵያ ስትፈረካከስና በ"ነበር" ስትቀር ማዬት ነው – የማይሳካ ምኞት። እናም ምኞታቸው ቅዥት ሲሆን ይተክናሉ፡፡ ይበግናሉ።… መለወጣችን ያማቸዋል፡፡ በተለይም የውስጥ የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ልክ እንደ አሁኑ ወቅት ሲበረቱባቸው የፀረ - ኢትዮጵያዊነት ጥላቻቸው ጫፍ ላይ ይደርሳል አሊያም ትዝ ይላቸዋል–ወጥረው የያዟቸውን ውስጣዊ ሀኔታዎች ለመርሳት ወይም ለማረሳሳት።

በእርግጥ አቶ ኢሳያስ ኢትዮጵያን ብቻ አይደለም ሲያምሱ የኖሩት፡፡ የማፍያ መንግስታዊ ዘመናቸውን ግማሹን ያህል በላዩን ያባከኑት ከጎረቤት ሀገራት ጋር እንደ አበደ ውሻ ያንንም ይንንም ሲናከሱና ቀጣናውንና ሞክረኝ በማለት ሲያሸብሩ ነው። እናም ጥፋትን የተጠማ ስብዕና እንደተጠናወታቸው በምግባራቸው አስመስክረዋል፡፡ ከመገለልና የአሸባሪነትን ማዕረግን ከመሸለም በስተቀር ተግባራቸው ሌላ ትርፍ ባያስገኝላቸውም፡፡

ሰሞኑን ወደ ግብፅ በማቅናት የግብፅ አድናቂ መሆናቸውን በመልዕክተኞቻቸው አማካኝነት ለማብሰር የሞከሩት አቶ ኢሳያስ፤ እርግጥም ጊዜ የማይሽራቸው የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት መሆናቸውን በአደባባይ አስመስክረዋል፡፡ ጊዜና አጋጣሚን እየጠበቀች ብቅ በምትልና አቅም በሌላት ተናዳፊ ተርብ እየተመሰሉ፡፡ ይሁንና ምንም እንኳን ይህን ለማለት ጊዜው ገና ቢሆንም፤ በአቶ ኢሳያስ ጭብጨባ ሞቆት የፀረ - ኢትዮጵያዊነት ትግላቸውን የሚቀላቀል ትውልድ በዛሬይቱ ግብፅ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ሰውዬው የሚችሉትን ያህል ርቀት ለመጓዝ ሞክረዋል– "ሩቅ አላሚ ቅርብ አዳሪ" እንደሚለው የሀገሬ ሰው፡፡ እንደ አቶ ኢሳያስ ፍላጎት ከሆነ ቢያንስ ፀረ - ኢትዮጵያዊነትን የሚሰብኩበት የሚያሰለጥኑበት የሚያስታጥቁበት ምቹ መደላድል ይፈልጋሉ–

በግብፅ፡፡ እናም እየደነጋገዘ ያለው ዘመናቸው እስከነአካቴው ሳይጨልም የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ወደ ማዶ ቢያማትሩ ወይም አዲስ ወዳጅ ለማፍራት ቢከጅሉ አይገርምም፡፡ ለምን ቢሉ የኤርትራ ነጻነት ሻዕቢያን እንጂ ኤርትራዊያንን ነጻ ስላላወጣ በዜጎቹ ውስጥ ተቀባይነት ማግኘት ባለመቻሉ ነው፡፡ በዚህ ሳቢያም ፀረ - ሻዕቢያ ትግል በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር እየጋመና እየተፏፏመ በመሆኑ ሰውዬው ይህን ምልከታ የሚያስቀይሩበት ቀሽም አካሄድን ቢመርጡ አይፈረድባቸውም። ጭንቀት የማያስደርገው ነገር የለምና!

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት አቶ ኢሳያስ ወደ ግብፅ እንዲያማትሩ ሶስት ዋና ዋና መሰረታዊ ምክንያቶች አስገድደዋቸዋል፡፡ ቀዳሚው ዕብሪተኛ ባህሪያቸው ነው፡፡ ጭፍን ጸረ - ኢትዮጵያዊነት አቋማቸው፡፡ ዕቅዳቸው የቀጣናው አውራ ሆነው ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት አካላቸው አድርገው ሃብቷን መመዝበርና ዜጎቿን ማስገበር ነበር፡፡ ዳሩ ግን የምስራቅ አፍሪካ ፖሊስ የመሆን ህልማቸው እንደ ጠል ደመና ድንገት በመክሰሙ ሁሉም ሃሳባቸው በሞኞች ብቻ ሊቀርባቸው ችሏል፡፡ እናም የአስመራው ጥገኛ መንግስት ከመሬት ተነስቶ ፀረ- ኢትዮጵያዊነትን ይደልቃል፡፡ ፀረ- ኢትዮጵያዊት ዜማ የሚነሽጣቸው ካሉም ተሰጥኦቸውን እንዲያወጡት ይመክራል፣ ያማክራል፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያን አንዲት ጋት እንኳን ከልማቷ ማስቀረት እንደማይቻለው ውስጡ ቢገነዘበውም፣ ይህን እኩይ ሴራውን የሙጥኝ ብሎ ይሰራል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሻዕቢያ የገንዘብ አቅሙ መዳከሙ ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ መገለሉን የሚታደግለት አውድና ለጥፋት ተልዕኮው የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኝበት ዕድል መፍጠሩ አይቀርም። ከፍ ሲልም በእርሱ ቤት ያልተበላባቸውን ስልቶች ማፈላለጉ የግድ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት በግብፅ ከትሞ አንዳንድ ፀረ - ኢትዮጵያ ሃይሎችን በማሰባሰብ አንድም ለብቸኝነቱ ወዳጅ ቢያፈላልግ አሊያም ምፅዋትን ቢያማትር አይገርምም፡፡ ግርግር ለሌባ ይመቻልና አጋጣሚውን ተቀምመው ለፀረ- ኢትዮጵያዊነት ወደዚያው የሚያቀኑ እንደ ግንቦት ሰባት ዓይነት የሽብር ህዋሶቹ ስለማይታጡ የአቶ ኢሳያስ መላ አዋጭ ባይሆንም ቢያንስ እዚያው ካይሮ ውስጥ ሊያዝቀዝዝም ይችላል ባይ ነኝ፡፡

የሻዕቢያን ህልውና ቋፍ ላይ የጣለው ኢትዮጵያን ለመተናኮል በገንዘብም ይሁን በወታደራዊ አቅም ደካማ መሆኑ እንዲሁም የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ለፀረ- ሠላም ኃይሎች ምቹነቱ እየቀነሰ በመምጣቱ ብቻ አይደለም፡፡ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኤርትራዊያን ለሻዕቢያ ያላቸው ጥላቻ ከምንጊዜውም የመረረ እየሆነ መምጣቱና ህዝባዊ ድጋፍ በማጣቱ ጭምርም ነው፡፡ ለወትሮው ከደጋፊዎቹ በሚያገኘው የሁለት በመቶ የዜጎች መዋጮ ገንዘብ ሽብርን የሚመራው፣ የሚያስለጥነውና የሚያስታጥቀው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር፣ የሁከት አጀንዳው ፍርጥርጥ ብሎ

በመታወቁ ሁሉም ዜጋው አይንህ ላፈር እያለው ነው፡፡ ወደ ግብፅ እንዲያቀና ያስገደደው ሶስተኛው ምክንያትም ይህ መሆኑ አያጠራጥርም።

የአስመራው የሁከት ቡድን አፋኝ፣ ፈላጭ ቆራጭና ፀረ - ዴሞክራሲያዊ መሆኑም በገዛ ዜጎቹ ሊጠላ ችሏል፡፡ አገዛዙ ኤርትራን በሰብዓዊ መበት ረገጣ ግንባር ቀደም ሀገር እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ሥርዓቱ በግለሰቦች የሚመራ ነው፡፡ ምርጫ ብሎ ነገር የለም፡፡ ግና እነዚህና ሌሎች መሰል ችግሮች ተደማምረው ወደ ገደል እየገፉት ያለው ሻዕቢያ፣ የውስጥ ጉዳዮንና እየሻገተ ያለውን ህልውናውን ለመሸፋፈን ብሎም የጥሞና ጊዜ ለማግኘት አዳዲስ የሞኝ ብልጣ-ብልጥነቶችን ይዞ ብቅ ማለቱ የሚጠበቅ ነው፡፡

ዳሩ ግን ሻዕቢያ የሆዱን በሆዱ ይዞ የግብጽ ወዳጅ መስሎ ለመቅረብ ቢሞክርም አዲሶቹ የግብፅ መንግስት ባለስልጣናት የሽብር ቡድኑን ባህሪ ጠንቅቀው ስለሚገነዘቡ የጥፋቱ መሪና ተባባሪ ሊሆኑ የሚችሉ አይመስለኝም፡፡ መሆንም አይገባቸውም። ምክንያቱም የአቶ ኢሳያስ የሽብር ቡድን ለምናልባቱ በማለት የህልውናውን ማቆያ የመጨረሻ ዕድል እየሞከረ በመሆኑና ዘመኑም ቢሆን በማምታታት የሚኖርበት እንዳልሆነ ስለማይጠፋቸው ነው፡፡ የአስመራው አስተዳደር አንድም በዓለም አቀፉም ይሁን በአፍሪካ ህብረት እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት (ኢጋድ) ተቀባይነት የሌለው፣ ሁለትም የገንዘብ ምንጩ የደረቀ፣ ሶስትም በሠራዊቱ ሳይቀር ጫና እየደረሰበት በመሆኑ ለካይሮ መንግስት የሚያደርግለት ጠብ የሚል ነገር አይኖርም፡፡ ይልቁንም የሙርሲ መንግስት ከዚህ ዓይነቱ ጠብ-አጫሪ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በቀጣናው ሀገራት እንዲጠላ ሊያደርገው ይችላል ባይ ነኝ።

እናም የሻዕቢያ ወቅታዊ አቋም ያን ያህል ተራቁቷል፡፡ ወደ ስልጣን የመጡት አዲሶቹ የግብፅ ባለስልጣናት በሻዕቢያ አጨብጫቢነት ሊታለሉ አይገባም፡፡ እንደ ሙባረክ የአገዛዝ ዘመን ወቅት ነጭ ለባሽ አሰልፎ ሀገራትን የማመስ እኩይ ተግባር መቼም ቢሆን እንደማይሰራ ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል። ከዚህ ይልቅ ኢትዮጵያና ሌሎቹ የናይል ተፋሰስ ሀገራት በሀብታቸው የመጠቀም መብት እንዳላቸው በመገንዘብ የጦረኛው አቶ ኢሳያስ ጠጋ ጠጋ ማለት ለማንም እንደማይበጅ ተረድተው ከእውነቱ ጎን መቆም ይኖርባቸዋል፡፡ እውነቱ ደግሞ ለዘመናት በመብታቸው ሳይጠቀሙ የኖሩት የተፋሰሱ ሀገራት ያለምንም ማቅማማት በደስታ የተቀበሉት ፍትሃዊውን የናይል ወንዝ አጠቃቀም የሚዳኘው ህግ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በናይል ወንዝ ላይ ታላቁን የህዳሴ ግድብ እየገነባች ያለችው የግብፅን ተጠቃሚነት ለመንፈግ አይደለም– የግብጽንም ይሁን የሌሎች የተፋሰሱን ሀገራት ፍትሃዊ የውሃ ክፍፍልና አጠቃቀም ዋስትና ከፍ የሚያደርግ አዲስ ህገ - ደንብ እንዲደነገግ በማድረግ እንጂ፡፡ የኢትዮጵያ ጥያቄ በጋራ ሀብታችን በጋራ እንጠቀም፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን አብረን እንደግ ነው፡፡

እናም በዚህ ፀሐፊ እምነት ፕሬዚዳንት ሙርሲ በዜጎቻቸውም ሆነ በዓለም አቀፉ ማህብረሰብ የተወገዘውን የአቶ ኢሳያስን ከንቱ ጦር አምላኪ ውዳሴ ወደ ቅርጫት ውስጥ ጥለው፣ በአባይ ጉዳይ ከራስጌው ተፋሰስ ሀገራት በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ቢወያዩ አትራፊ ይሆናሉ፡፡ ለግብጽም ሆነ ለተፋሰሱ ሀገራት የሚበጀው መነጋገሩና ይበልጥ መቀራረቡ እንጂ፤ በየመንደሩ እየዞረ በተላላኪነት ባዶ ኮሮጆውን ለመሙላት የሚቀባጥርን የሽብር ቡድን በማስጠጋት አይደለምና፡፡

እርግጥም አቶ ኢሳያስና ፕሬዚዳንት ሙርሲ ሃቁን ደፍጥጠው የተፋሰሱ ሀገራት የተስማሙበትንና አለም አቀፍ የውሃ ህግ ሙሉ በሙሉ የሚደፍሬውንና ፍትሃዊውን የናይል ወንዝ አጠቃቀም ህገ -ደንብ ቢቃረኑ ለማንም አይበጅም፡፡ ኢ- ፍትሃዊና ኢ- ሞራላዊ ነው፡፡… ምንም ሆነ ምን አንድ ሃቅን መዘንጋት የለበትም፡፡ እርሱም በእኔ እምነት ምንም እንኳን የግብፅ መንግስት በአቶ ኢሳያስ የጥፋት ምክር ተወናብዶ አዋጭ ያልሆነውን አቅጣጫ ይከተላል ባይባልም፤ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ግን የሚጠብቃቸው የቤት ሥራ ሊኖር ይችላል፡፡ በመሆኑም ምናልባትም ሴራ ከተፈጠረ በመከታተልና በተለይም የሻዕቢያን የጥፋት ዕቅዶች ለማምከን ጠንከሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡ እርግጥ የአቶ ኢሳያስንና የአንዳንድ ፀረ - ሰላም ኃይሎችንና አሸባሪዎችን ሴራ መመከት የኢትዮጵያ ድርሻ ብቻ አይደለም፡፡ የተፋሰሱ ሀገራት ይበልጥ አንድ በመሆን መብታቸውን ለመንፈግ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን እየተከታተሉ በእንጭጩ ማስቀረት ይኖርባቸዋል– ምንም እንኳን ህጉን የሚቀለብስ ተዓምር ይፈጠራል ተብሎ ባይጠረጠርም፡፡

የቅኝ ግዛት ህግ በማንኛውም መስፈርት ቢመዘን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ይህን ህግ እንደ መብት ለግብፅ የሰጠቻት የያኔዋ የሀገሪቱ ቅኝ ገዥ የነበረችው እንግሊዝ ናት– በናይል ወንዝ አማካኝነት ጥጥ እያመረተች የግብፅን ሀብት ለመመዝበር፡፡ ግና ምናልባት ግብፅና ኤርትራ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ህግን ተቀባይነት ያለው አድርገው የሚወስዱ ከሆነ አስቸጋሪ ነው፡፡ ግብፅን ብቸኛ ተጠቃሚ አድርጎ የሸለመው ኢ- ፍትሃዊ ህግ ትክክል ይሆናል ማለት ነው፡፡ እናም የዘመነ ቅኝ አገዛዝ ህጎች ተቀባይነት አይኖራቸውምና መሻራቸው አማራጭ ብቻ ሳይሆን የህልውናም ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው ኢትዮጵያም ይህንን ኢ- ፍትሃዊና ኢ-ምክንያታዊ ህግ በመቃወምና በመብቷ ለመጠቀም በመወሰን የህዳሴውን ግድብ በመገንባት ላይ ያለችው፡፡

ሆኖም ከግብፅ ጋር ወግኖ ፀረ- ኢትዮጵያዊነትን ለማቀንቀን ቆርጦ የተነሳው ሻዕቢያ ለመደፍጠጥ የፈለገው የኢትዮጵያን በአባይ ወንዝ የመጠቀም መብት ብቻ አይደለም– የተፋሰሱን የራስጌ ሀገራት በናይል የመጠቀም መብትም ጭምር እንጂ። እናም ሀገራቱ ከኢትዮጵያ ጋር ተሰልፈው የሻዕቢያን ሴራ ለማክሸፍ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እርግጥ ሻዕቢያ ጀሌዎችን እያሰለጠነና እያስታጠቀ ወደ ቀጣናው ከማሰማራት በዘለለ ሌላ የገዘፈ ጉዳት እንደማያመጣ ግልፅ

ነው፡፡ ተፅዕኖ ፈጣሪነቱ ከመረበሽ አይዘልም፡፡ ያም ቢሆን ግን የቡድኑ ዋነኛ ዓላማ ተያይዞ ለመጥፋት በመሆኑ የተፋሰሱ ሀገራት ተቀራርበው በመስራት የሁለቱ ሀገራትን አዲስ ሽርክና መከታተልና ሻዕቢያ እንደ ተላላኪነት የሚያገለግል ከሆነ "ሳይቃጠል በቅጠል" በማለት ሊቃጡ የሚችሉ ሙከራዎችን በእንጭጩ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ዳሩ ግን በአንድ ነገር መግባባት እንችላለን፡፡ ሻዕቢያ ከማንም ጋር ይወግን ከማን፣ የተፋሰሱ ሀገራት ከደረሱበት ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም ስምምነትና መብታቸውን ከመጠቀም የሚያግዳቸው አንዳችም ህግ የሌለ መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል። በተለይም ሀገራችንን በመብቷ እንዳትጠቀም የሚያግዳት ሃይል ከፀሐይ በታች እንደማይኖር ማወቅ አለበት።

አንድ ነጥብ ላክል። ምናልባትም የአቶ ኢሳያስ ሰሞነኛው የግብፅ ቁርኝት እንዳለፈው የሙባረክ ዘመን ሁሉ አዲሱንም የሙርሲ መንግስት በማታለል እና በሌለ አቅሙ 'ጦር ሰባቂ ነኝ' በማለት የወደቀ አኮኖሚውንና ፖለቲካውን ለመደገፍ ሊጠቀምበት ፈልጎ ከሆነ በእጅጉ መሳሳቱን መገንዘብ ይኖርበታል። እንዲያውም ይህ እኩይ ምግባሩ መቀመቅ ከተቶት የኪሳራዎች ሁሉ ኪሳራን ሊከናነብ ይችላል። ለዚህ ደግሞ ሁለት ምክንያቶችን ልጠቅስ እችላለሁ። አንደኛው አሁን ያለው የግብፅ ሁኔታ ጉዳይ ማስፈፀሚያ እያሉ ዶላር የሚታፈስበት አለመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ለእያንዳንዱ ሻዕቢያዊ-ወለድ ትንኮሳ ተመጣጣኝ እርምጃ ስለሚወስድና ይህ ደግሞ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ እስከ ማድረግ የደረሰውን የሀገሪቱን ሠራዊት ይበልጥ የሚከፋፍል መሆኑ ነው። እስቲ እነዚህን ሃቆች በጥቂቱ ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው።…

እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት በግብፅ ውስጥ ያለው አጠቃላይ የፖለቲካ ትኩሳት የተረጋጋ አሊያም የሰከነ አይደለም። በዚያች ሀገር የተቀጣጠለው ፖለቲካዊ ትኩሳት ለመብረድ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል በርካታ ተንታኞች ይናገራሉ። ከሙባረክ ውድቀት በኋላ በሀገሪቱ የሚታዩት ክስተቶች ዜጎችን ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ የሚያሰገቡ ሊሆኑ አልቻሉም። በፕሬዚዳንት ሙርሲ ደጋፊዎችና በተቃዋሚዎቻቸው መካከል ሳያሰልስ በየጊዜው የሚነሳው እሰጥ አገባ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እየጎዳው ነው። እያናጋው ነው ሊባልም ይችላል። ይህ ደግሞ ጦረኛው አቶ ኢሳያስ ለሚያልሙት በጥገኝነት ኮሮጆአቸውን የመሙላት አባዜ እምብዛም የሚመች አይመስለኝም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እርሳቸው እንዳሰቡት ወደ ልመና አኩፋዳቸው የሚገባ ነገር ሊኖር አይችልም፣ቢኖርም ረብ ያለው ነገር አይሆንም። በዚህም ምክንያት አቶ ኢሳያስ የተሳሳተን የልመና በር እያንኳኩ ነው ማለት ይቻላል።

ከኢትዮጵያ አንፃርም ቢሆን፣ በአቶ ኢሳያስ አስተዳደር አማካኝነት ለሚፈፀሙ ማናቸውም ተግባራት ራስን የመከላከል ህጋዊና ተመጣጣኝ እርምጃ መወሰዱ አይቀርም። እንዳለፉት ጊዜያት

ሻዕቢያ በሀገራችን ላይ የሽብር ትንኮሳ ሲፈፅም ዝም ተብሎ አይታይም። እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ ወደፊትም ለእያንዳንዱ እኩይ ተግባሩ በራሱ ቋንቋ ምላሽ ይሰጠዋል። ይህን ደግሞ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሰሞኑን ለኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረቡት የስምንት ወራት ሪፖርት ላይ በይፋ አረጋግጠውታል። ምናልባትም የአስመራው ነውጠኛ ቡድን የነጭ ለባሽነት ተግባሩን ወደፊት ቢከውን፤ ከኢትዮጵያ በኩል በሚሰጠው የአፀፋ ምት ሳቢያ በአሁኑ ወቅት ተከፋፍሎ በቋፍ ላይ ያለው የኤርትራ ሰራዊት የከፋ አደጋ ሊጋጥመው ይችላል። ይህ ደግሞ ሻዕቢያ ወደ ማይወጣው አዘቅት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል። እናም በዚህም አለ በዚያ አቶ ኢሳያስ የኢትዮጵያን ህዝብ ልማት አስተጓጉላለሁ ብሎ ከልመና ባልተናነሰ ሁኔታ ከግብፅ ጋር የጀመረው አዲስ ቁርኝት አያዋጣውም–መዘዝ ያመጣበታል እንጂ።…እናም ሻዕቢያ እንኳንስ የኢትዮጵያ ህዝብ በስስት ዓይን የሚመለከተውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ ቀርቶ አንዳች ተራ ትንኮሳን ካሰበ “አላርፍ ያለች ጣት…” የሚለውን ብሂል ማስታወስ ይኖርበታል።